Temari.et

# Civics and Ethical Education, 2012 EC, Grade 8 model exam

Grade 8 · Citizenship Education · 2012 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 55 **Total marks:** 55

Name ______________ Grade ______ ID No. ______ Date ______

**1.** ከሚከተሉት ዲሞክራሲያዊ መርህ ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

**A.** የህግ የበላይነት መርህ
**B.** የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ
**C.** የአናሳዎች ድምፅ የበላይነት
**D.** የብዙሃን ድምፅ መከበር

**2.** ከሚከተሉት መካከል ዲሞክራሲያዊ መብት የሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** በመረጡት አከባበር መኖር
**B.** ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ
**C.** በመረጡት ስራ ዘርፍ መስራት
**D.** በህይወት የመኖር መብት

**3.** ስልጣን በማዕከል ብቻ ተይዞ የሚመሰረት የመንግስት ስያሜ ምን ይባላል? (1)

**A.** ፌደራላዊ
**B.** አሀዳዊ
**C.** ኮንፌዴሬሽን
**D.** ዲሞክራሲያዊ

**4.** የሃሳብ ልዩነት በሚከሰትበት ወቅት ጥሩ የመግባባት መንፈስ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ከሚከተሉት የትኞቹ ናቸው? (1)

**A.** አለመቻቻል ፣ ውይይት፣ መደማመጥ
**B.** ውይይት፣ መደማመጥ፣መቻቻል
**C.** አለመደማመጥ፣ መቻቻል፣ውይይት
**D.** አለመወያየት፣ መቻቻል፣ አለመደማመጥ

**5.** ከሚከተሉት በፌዴራልና በክልል የመንግስታት አወቃቀር ስርዓት ውስጥ የሚመደቡ የስልጣን አካላት የትኞቹ ናቸው? (1)

**A.** ህግ አውጪ፣ህግ አስፈፃሚ፣ህግ ተርጓሚ
**B.** የህግ መወሰኛ፣ የህግ መምሪያ፣ ህግ ተርጓሚ
**C.** የህግ ተርጓሚና የህግ መምሪያ
**D.** ህግ አውጪና ህግ አስፈፃሚ

**6.** የህዝብ አገልጋይ ባለስልጣናት ሊላበሱት የሚገባቸው የመልካም ስነ-ምግባር መገለጫ የቱ ነው? (1)

**A.** አድሎ መፈፀም
**B.** ስልጣንን በአግባቡ አለመጠቀም
**C.** ለህዝብ ጥያቄ መልስ መስጠት
**D.** ለህግ አለመገዛት

**7.** በሰዎች መካከል በቃልኪዳን ተጠብቆ የሚያዝ ድርጊት የሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** መልካም ስነ-ምግባር
**B.** ታማኝነት
**C.** ሚስጢር
**D.** ወዳጅነት

**8.** ከሚከተሉት የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብት መከበሩን የሚገልፀው ሃሳብ የቱ ነው? (1)

**A.** በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም
**B.** ባህላቸውን እንዳይገልፁ ማድረግ
**C.** እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተድሩ ማድረግ
**D.** ታሪካቸውን እንዳይንከባከቡ ማስቻል

**9.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ- መንግሰስት ድንጋጌ መሰረት የሴቶች የእኩልነት መብት መካከል የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

**A.** ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ ማግኘት
**B.** ንብረት ማፍራት
**C.** ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነፃ መሆን
**D.** ጋብቻን በቤተሰቦቿ ፍላጎት መመስረት

**10.** የአካል ጉዳተኞች የእኩልነት መብት ሲከበር ለሀገር የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ምንድነው ? (1)

**A.** በልመና ተግባር ላይ መሰማራት
**B.** ምፅዋትን መጠየቅ
**C.** ከጥገኝነት አስተሳሰብ አለመላቀቅ
**D.** አቅማቸውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም በልማት መሳተፍ

**11.** ፍትሀዊነት ምን ሊገልፅ ይችላል ? (1)

**A.** ፍርድን ማጣመም
**B.** በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ልዩነትን አላግባብ እንዳይፈጠር መከላከል
**C.** ማንኛውም አይነት ልዩነት አለማስተናገድ
**D.** ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ መሆን

**12.** ዜጎች ባላቸው የሀብት ይዞታ ነግደው ባገኙት የትርፍ መጠን ተገናዝቦ የሚተመንበት ስርዓት ምንድነው? (1)

**A.** መዋጮ
**B.** ግብር
**C.** ወለድ
**D.** የመጠባበቂያ በጀት

**13.** የሀገርን ገፅታ ከሚጎዱ አፍራሽ ተግባራት መካከል አንዱ የቱ ነው ? (1)

**A.** ሙስናና የኮንትሮባንድ ንግድ መጥፋት
**B.** ለጥቅም ሲባል ዕውነታን አዛብቶ ለህዝብ አለማቅረብ
**C.** ግብርን በወቅቱ መክፈል
**D.** የእርስ በርዕስ ጦርነት

**14.** ህጋዊ ወይም ህሊናዊ ተጠያነት ያለው ጽንስ ሀሳብ ሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** የህዝብ ሉአላዊነት
**B.** ጠንካራ የስራ ባህል
**C.** የሃላፊነት ስሜት
**D.** ቃልኪዳን

**15.** የጋራ ሃላፊነትን የመወጣት ጥቅም ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** ብዙ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል
**B.** ስራን ያቀላጥፋል
**C.** በሰዎች መካከል ግጭት ይፈጥራል
**D.** ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎን ያሳድጋል

**16.** ለሀገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት እንቅፋት ያልሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** ጥገኝነትን አምኖ መቀበል
**B.** ሳይሰሩ መኖርን አለመፀየፍ
**C.** ጠንካራ የስራ ባልን ማዳበር
**D.** ልመናና እንደገቢ ምንጭ መቁጠር

**17.** ራስን መቻል ከሚለው ፅንስ ሀሳብ ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ? (1)

**A.** የራስን ጠንካራና ደካማ ጎን ማወቅ
**B.** የምንሰራውን ስራ በራስ አቅምና ችሎታ መስራት
**C.** የራስን አቅምና ችሎታ ለይቶ ማወቅ
**D.** የጠባቂነት ስሜትን ማዳበር

**18.** ከማንኛውም የፖለቲካ ፣ ወታደራዊ እና ሐይማኖታዊ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የሚቋቋም ማህበር የቱ ነው ? (1)

**A.** የሲቪክ ማህበር
**B.** ወታደራዊ ማህበር
**C.** የፖለቲካዊ ማህበር
**D.** ሐይማኖታዊ ማህበር

**19.** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የልማት ዓላማዎችን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ? (1)

**A.** ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ
**B.** የጥቂት ግለሰቦችን ኢኮኖሚ ማሳደግ
**C.** ፈጣን ኢኮኖሚ እድገት ማምጣት
**D.** የህዝብን ፍላጎት ማሟላት

**20.** በኢ.ፊ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት አንቀፅ 11 ተደነገገው (1)

**A.** ሐይማኖታዊ መንግስት መመስረት
**B.** መንግስት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ይገባል
**C.** መንግስትና ሐይማኖት የተነጣጠሉ ናቸው
**D.** ሐይማኖት በመንግስት ጉዳይ ላይ ጣልቃ ይገባል

**21.** ከዜጎች ባህሪያት ውስጥ ለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተዋፅኦ የሌለው የቱ ነው ? (1)

**A.** ግለኝነት
**B.** ተግባራዊነት
**C.** ፍቃደኝነት
**D.** ተነሳሽነት

**22.** ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በሀገራችን የትኛውን ህብረተሰብ ክፍል በይበልጥ ያጠቃል? (1)

**A.** ሕፃናትን
**B.** ወጣቶችን
**C.** አዛውንትን
**D.** አረጋውያንን

**23.** በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር ከሚረዱ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የቱ ነው? (1)

**A.** የራስ ችሎታን ያለማወቅና ያለማበልፀግ
**B.** የሌላውን ሀሳብ ያለማክበር
**C.** እውነታን በፀናት መቀበል
**D.** እቅድን ያለማውጣትና ስራን ያለመገምገም

**24.** ከሚከተሉት ለቅርሶች መበላሸት መንስኤ ከሆኑት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

**A.** የእሳት ቃጠሎና ጦርነት
**B.** እድሳትና እንክብካቤ ማድረግ
**C.** የትምህርት እጦት
**D.** አስከፊ ድህነት

**25.** ከሚከተሉት ከአውቀት፣ ከኢኮኖሚ እና ከማህበራዊ ጥገኝነት ተላቆ ነፃ መሆንን የሚያመለክት ፅንስ ሀሳብ የቱ ነው (1)

**A.** ራስን መቻል
**B.** ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ
**C.** የቁጠባ ባህል
**D.** በራስ መተማመን

**26.** ቁጠባ ማለት ምን ማለት ነው ? (1)

**A.** ዛሬን እየተቸገሩ ለነገ ማስቀመጥ ነው
**B.** ከዕለት ፍጆታ ላይ ቀንሶ ማስቀመጥ ነው
**C.** በስራ የተገኘውን ገቢ በሙሉ መጠቀም ነው
**D.** በስራ የተገኘውን ገቢ በሙሉ ማስቀመጥ ነው

**27.** ከሚከተሉት የእውቀት አገልግት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ? (1)

**A.** ለምርምር አገልግሎት
**B.** ለፈጠራ ሥራ ይጠቅማል
**C.** በዜጎች መካከል የሃሳብ ልዩነት ይፈጥራ
**D.** ለሀገር እድገት ወሳኝ ይሆናል

**28.** ኋላቀር አስተሳሰብን ለማስወገድ ከሚያግዙ ሁኔታዎች የሚመደበው የቱ ነው ? (1)

**A.** ጎታች አመለካከቶችን ማራመድ
**B.** በስሜት ላይ የተመረኮዘ አስተያየት መስጠት
**C.** በጭፍን አመለካከቶች መመራት
**D.** በእውቀትና በምክንያታዊ የተደገፈ መሆን

**29.** ከሚከተሉት መርህ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚቆምበት ምሰሶ የቱ ነው ? (1)

**A.** ነፃ የፖለቲካ ስልጣን ውድድር
**B.** የህግ የበላይነት
**C.** ግልፅነትና ተጠያቂነት
**D.** የብዙሃኑ ድምጽ የበላይነትና አነስተኛው መከበር

**30.** ከግለሰብ ሰብአዊ መብቶች መካከል የሚመደበው የቱ ነው? (1)

**A.** የእኩልነት መብት
**B.** የሐይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት
**C.** በአካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብት
**D.** የመዘዋወር ነፃነት

**31.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ህግ አስፈፃሚ አካል ማን ነው? (1)

**A.** የሚኒስትሮች ምክር ቤት
**B.** ጠቅላይ ፍርድ ቤት
**C.** የተወካዮች ምክር ቤት
**D.** የክልል መስተዳድር

**32.** ከቡድን ዲሞክራሲያዊ መብቶች መካከል የማይመደበው የቱ ነው? (1)

**A.** የህዝብ ሉአላዊነት
**B.** የመደራጀት መብት
**C.** በህይወት የመኖር መብት
**D.** የመሰብሰብ መብት

**33.** በመንግስት ባለስልጣናት ላይ የስልጣን ገደብ መጣል ያስፈለገው (1)

**A.** ህብረተሰቡ ተገቢ አገልግሎት እንዲያገኝ
**B.** አድሎአዊ አሰራሮችንና ህገወጥነትን ለማበረታታት
**C.** የዜጎችን ሰበዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጣስ
**D.** ባለስልጣናት በስልጣናቸው እንደፈለጉ እንዲጠቀሙ ለማድረግ

**34.** በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለህይወታቸው ለንብረታቸው ህጋዊ ጥበቃ ዋስትና መስጠት ማለት ነው (1)

**A.** የስልጣን ገደብ
**B.** ፍትህዊነት
**C.** የህግ ከለላ
**D.** ሀቀኝነት

**35.** የበጀት ጉድለትን ለማተካከል የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ሆነው የቱ ነው? (1)

A. ድጎማ
B. ግብር
C. ጉቦ
D. ቁጠባ

**36.** ለሀገር ልማት አፈፃፀም ውጤታማነት መንግስት የሚያወጣው ህግ፣ የሚደነግገው ደንብና መመሪያ (1)

A. ህገ-መንግስት
B. አዋጅ
C. ዕቅድ
D. ፖሊስና እስትራቴጂ

**37.** ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በአስተማማኝ የመከላከያ ዘዴ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. ኮንዶም መጠቀም
B. በአንድ መወሰን
C. ከጋብቻ በፊት ወሲብ አለመፈፀም
D. የደም ንክኪን ማስወገድ

**38.** ሰዎች ሙስና እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው ነገር ምን ሊሆን ይችላል? (1)

A. የተሻለ ደመወዝ ማግኘታቸው
B. ፍላጎታቸው ሲሟላላቸው
C. ስልጣናቸው ሲገደብ
D. ሀላፊነት ሲጎድላቸው

**39.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ህግና ደንብ ማውጣትና ማፅደቅ የማን ስልጣን ነው? (1)

A. የተወካዮች ምክር ቤት
B. የፌዴሬሽን ምክር ቤት
C. የሚኒስትሮች ምክር ቤት
D. የዳኞች ጉባኤ

**40.** ከሚከተሉት መካከል የፌዴራልና የክልል መንግስታት አንድነትን የሚያሳየው (1)

A. የስልጣን አወቃቀራቸው ተመሳሳይ መሆኑ
B. አዲስ አበባን በጋራ ማስተዳደር
C. ገንዘብና መከላከያ ሰራዊትን በጋራ መስተዳደር
D. በሁለቱም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መኖር

**41.** የፌዴራል የመንግስት አስተዳደር ከሌሎች የመንግስት አስተዳደሮች የሚለየው ዋነኛ ባህሪው የትኛው ነው? (1)

A. ሥርዓቱ በህግ የበላይነት የሚመራ ነው
B. በፌዴራል መንግስት እና በክልል መንግስታት መካከል የሚኖር የስልጣን ክፍፍል
C. የተጠያቂነት ሥርዓት መኖር
D. ፕሬዝዳንታዊ መንግስት አስተዳደር መኖር

**42.** የኢትዮጲያ የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ምንን መሰረት ያደረገ ነው? (1)

A. የህዝብን ጥቅም ማስቀደም
B. የባለስልጣናትን ፍላጎት መሰረት ማድረግ
C. ኢኮኖሚን ብቻ መሰረት ማድረግ
D. ላደጉት ሀገራት መንግስት መቆምን

**43.** ህገ መንግስት ምንድን ነው? (1)

A. የወንጀለኛ መቅጫ ህጎችን የያዘ ነው
B. ሰበአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ብቻ የያዘ ህግ ነው
C. የመንግስትን ታሪክ የሚያብራራ ሰነድ ነው
D. የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው

**44.** ዕውቀትን ለማዳበር በተጨባጭ የሚረዳው (1)

A. የስራ ዕቅድ
B. ህልም
C. በስራ የማይተረጎም ምኞት
D. የተሰበሰቡ መረጃዎች

**45.** አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው? (1)

A. አካል ጉዳተኞች ማንኛውም ሰው ያለውን ግዴታ እና መብት አሏቸው
B. አካል ጉዳተኞች መብት እንጂ አገራዊ ግዴታ የለባቸውም
C. የአካል ጉዳተኞች መብት እንዲከበር ሁሉም ዜጋ ሀላፊነት አለባቸው
D. አካል ጉዳተኞች ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ማከናወን ይችላሉ

**46.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት አንድ ሰው ወንጀለኛ ነው የሚባለው እንዴት ነው ? (1)

**A.** ፖሊስ ክትትል ሲያደርግበት
**B.** ፖሊስ በጥርጣሬ ሲይዘው
**C.** እጅ ከፍንጅ ሲያዝ ወይም በምስክሮች ሲረጋገጥ
**D.** ፖሊስ በቁጥጥር ስር ሲያውለው

**47.** ሙስናን ለማስወገድ የኢትዮጲያ መንግስት እና ህዝብ በዋነኝነት ማድረግ ያለባቸው (1)

**A.** የፀረ ሙስና ኮሚሽንን ማጠናከር
**B.** የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት መስራት
**C.** ድህነትን ማጥፋት
**D.** የወንጀለኛ መቅጫ ህግን ማጠናከር

**48.** አንድ ሰው መብቱን ሲጠይቅ ምን አሟልቶ መገኘት አለበት (1)

**A.** ግዴታውን
**B.** ድርሻውን
**C.** ፍላጎቱን
**D.** ቃልኪዳኑን

**49.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ስለምን ደንግጓል? (1)

**A.** የመደራጀት መብትን
**B.** የሴቶች መብትን
**C.** ፍትህ የማግኘት መብትን
**D.** የዜጎች እኩልነት መብትን

**50.** አንድ ታሪክ ትክክል ነው የሚባለው መቼ ነው? (1)

**A.** ፀሐፊው በራሱ ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ሲፃፍ
**B.** በመንግስት ባለስልጣናት ፍላጎት ሲፃፍ
**C.** ትክክለኛ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ሲፃፍ
**D.** አንድን ብሄርን መሰረት አድርጎ ሲፃፍ

**51.** ዜጎች ፍትህን ለማስከበር ሲሉ መጠቀም የሌለባቸው ድርጊት የቱ ነው? (1)

**A.** ፍርድ ቤትን መጠቀም
**B.** ለፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ
**C.** ጉልበት መጠቀም
**D.** ባህላዊ የፍትህ አካላት

**52.** በኢ.ፊ.ዴ.ሪ መንግስት ህግ አስፈፃሚ አካል ያልሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** የጤና ሚኒስቴር
**B.** የመከላከያ ሚኒስቴር
**C.** የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
**D.** የትምህርት ሚኒስቴር

**53.** አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው (1)

**A.** በጦርነት ላይ መሳተፍ
**B.** ጠንክሮ መማር
**C.** የህይወት መስዋትነት ማድረግ
**D.** ተጋድሎ መፈፀም

**54.** የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት የአኗኗር ዘይቤን የሚገልፅ ነው (1)

**A.** ባህል
**B.** ሐይማኖት
**C.** እምነት
**D.** አመለካከት

**55.** ከሚከተሉት መካከል ስለ ፌዴራል ህገ-መንግስት ትክክል ያልሆነው (1)

**A.** ሁለት ምክር ቤቶች አሉት
**B.** አስራ አንድ ምዕራፎች ይኖሩታ
**C.** 106 አንቀፆች አሉት
**D.** የተዘጋጀው በ1989 ዓ.ም ነው

— END OF EXAMINATION —